የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፲፫
አዲስ አበባ የካቲት ፪ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

29th Year No 13
ADDIS ABABA 9th February, 2023

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፹፩/፪ሺ፲፭

ለሥርዓተ ምግብ ማጠናከሪያ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፉ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ……………………………….ገጽ ፲፬ሺ፮፻፶፪

## Content

Proclamation No. 1281/2023

International Development Association Loan Agreement for Financing Food Systems Resilience Program Ratification Proclamation ……………………………….................Page 14652

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፹፩/፪ሺ፲፭

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ለሥርዓተ ምግብ ማጠናከሪያ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ሁለት መቶ ዘጠና ሰባት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር. (፪፻፺፯ ሚሊዮን ፮፻ሺ ኤስ.ዲ.አር) ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ሰኔ ፲፯ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

### PROCLAMATION NO. 1281/2023

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION**

**WHEREAS,** the Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association shall provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan an amount equivalent to Two Hundred Ninety-Seven Million Six Hundred Thousand Special Drawing Rights (SDR 297,600,000) for financing Food Systems Resilience Program was signed in Addis Ababa on 24th Day of June, 2022;

ይህንኑ ስምምነት የኢፌድሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ፮ኛ መደበኛ ስብሰባው ህዳር ፲፭ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለሥርዓተ ምግብ ማጠናከሪያ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፉ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፹፩/፪ሺ፲፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ሰኔ ፲፯ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 7156-ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ሁለት መቶ ዘጠና ሰባት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር. (፪፻፺፯ ሚሊዮን ፮፻ሺ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said agreement at its 6th ordinary session held on 24th Day of November, 2022;

**NOW, THERFORE**, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Federal Democratic Republic of Ethiopian Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Loan Agreement for financing Food Systems Resilience Program Ratification Proclamation No. 1281/2023".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement Number 7156-ET signed in Addis Ababa on 24th Day of June, 2022 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan an amount equivalent to Two Hundred Ninety-Seven Million Six Hundred Thousand Special Drawing Rights (SDR 297,600,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት ፪ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force up on its publication in the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa, On this 9th Day of February, 2023.**

**SAHLE-WORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**